


# የአቶ ኃይሌ መኩሪያ ሃ/ገብርዔል አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ ኃይሌ መኩሪያ ሃ/ገብርዔል ከአባቱ ከአምሣ አለቃ መኩሪያ ሃ/ገብርዔል እና ከእናቱ ከ ወ/ሮ የንጉሥነሺ ፈረደ መስከረም ፲፩ቀን 1953 ዓ.ም በጎንደር ክ/ሃገር አላር ከተማ ተወለደ።

እድሜው ለትምህርት እንደደረሰ በጎንደር ክ/ሃገር በጭልጋ አውራጃ በአይከል ከተማ በሰራግ ት/ቤት ከ፩ኛ እስከ 8ተኛ ከፍል ተማረ ከዚያም አይከል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርቱን እየተከታተለ ሳለ በወቅቱ በነበረው የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ የነበረውን መንግሥት በመቃወም ትምህርቱን አቋርጦ ከወጣት ጓደኞቹ ጋር በመሆን በ አካባቢው የትጥቅ ትግል ሲያደርግ ከነበረወ ከ ኢሕአፓ ሠራዊት ጋረ በመቀላቀል በወታደራዊና የሕክመና ሙያ በመሰልጠን ለ ዴሞክከራሲና ለፍተሀ በሚደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ በቆራጥነት አበርክቷል።

ከሁለት ዓመት መራራ ትግል ብኋላ ወደ ሱዳን ተሰደደ።በሱዳን ሦስት አመት ከቆየ በኋላ ወደ አሜሪካ አመራ፤በአሜሪካ የመጀመሪያዎቹ አመታት በቴክሳስ እስቴት በሂውስተን ከተማ በሜካኒክነት ትምህርት ሰልጥኖ ወጣ ከዚያም ወደ ዋሺንግተን ዲሲ አካባቢ በመምጣት ኑሮውን ጀመረ።

አቤ ! በመባል የሚታወቀው ኃይሌ በዋሽንግተን አካባቢ በኖረበት ዘመን ከባለቤቱ ከ ወ/ሮ ደባከ መኩሪያ  ቴወድሮስ ኃይሌንና  ቅድስት ኃይሌን በማፍራት ልጆቹን በማስተማር በፍቅርና በመንከባከብ ሲያሳድጋቸው ቆይቷል።

አቤ በማሕበረሰቡ እጅግ በጣም ተወዳጅ፤ለተቸገረ ፈጥኖ ደራሽ የነበረና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በተለይም አገሩን ኢትዮጵያን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ዛሬም እንደትናንቱ ዴሞክሪሲና ፍትህ እንዲሰፍን ለማድረግ የሚገባውን በሚፈለግበት ቦታ ሁሉ በመድረስ ጉልበቱን፤ገንዘቡን እንደሰጠ የኖረ ነው።

አቤ ለልጆቹ የነበረው ምኞት ኮሌጅ ጨርሰው ከዚያም ለቁምነገር ደርሰውለት ለማየት ነበር።ይሁን እንጂ ፈጣሪ አምላኩ በፈለገበት ጊዜ ለመጓዝ በጣም ባጭር ጊዜ ታሞ ህክምና ሲደረግለት ከቆየ በኋላ ኅዳር 25 ቅን 2005 ዓም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየን።

የአቤ መሞት ለቤተሰቡም ጭነ ለጓደኞቹ መሪሪ ሀዘን ነው። በዚህ የችግር ጊዜ ያለመስልቸት ተመላልሳችሁ ለጠየቃችሁትና በኃዘናችን ላይም በመገኘት ላጽናናችሁን ሁሉ መላው ቤተሰቡና ልጆቹ ምስጋናቸው ከፍ ያለ ነው።

የኃይሌን ነፍስ ፈጣሪ አምላካችን ከጎኑ እንዲያስቀምጣት ፅሎታችን ነው።